# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 316 ግንቦት 22 2006


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 20 ድል መቀሌ ውስጥ የአፓርታይድ ሠፈር የገነቡ የሥርዓቱ ቅምጥሎች፤ አዲስ አበባ ውስጥ የመቀሌ ሠፈር ተብሎ የተሰየመውን ህንጻ ያሳነጹ ሌቦች፤ በጋምቤላ፤ በአፋር፤ በቤነሻንጉልና ማሃል ኦሮሚያ የእርሻ መሬት እየዘረፉ የተቀራመቱ ህወሃቶችና የጥቅም ተካፋዮች እንጂ የሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አለመሆኑን በተግባር ለማሳየት ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን የወያኔን የአገዛዝ ሥርዓት ከላያችን ላይ አሽቀንጥረን ለመጣል ከምንጊዜውም በላይ መነሳት ያለብን ጊዜው አሁን ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የፋሺስቶች ቀን በፋሺስቶች ተከብሮ ዋለ

አገራችን ኢትዮጵያን ወድብ አልባ በማድረግ፣ መሬታችንን ለባዕድ በማስረከብ፣ የኢትዮጵያን ሃብትና ንብረት በመመዝበርና ከሃገር በማሸሽ፣ አርሶ አደሩን በማፈናቀልና መሬቱን ለባዕዳንና ለአገዛዙ ቅጥረኞች በመቸብቸብ፣ ለአገሬ ያገባኛል ያለውን ዜጋ ሁሉ በመግደልና በማስር..... እየተጓዘ እነሆ ፋሽስቱ ህወሓት ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ከያዘ 23 የጨለማ ዐመታት ተቆጠሩ። የልማት አርበኛ የዲሞክራሲ ጀግና እያለ ራሱን የሚጠራው ፋሽስቱ ሕወሓት.... አምባገነናዊ የጎሳ ፖለቲካውን በመርጨት አንዱን ዘር ከሌላው ዘር ጋር በማጋጨትና በርካታ የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን መፈጸም ከጀመረ 23 አመት ቢቆጠሩም አንዳች የልማት እና የዲሞክራሲ ብልጭታወችን ለማየት ሳንታደል፡ ጭቆና ድህነትና ረሃብ በአገሪቱ ነግሶ፤ የሰብአዊ መብት ጥሰቱ ከመቸውም ጊዜ በላይ ተባብሶ፤ የነጻ ፕሬሱ ተቀብሮ፤ እስር ቤቶች በመቶ ሺህዎች በሚቆጠሩ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ እስረኖች ተጥለቅልቀው፤ የፍትህ አካላት በፋሽስቱ ወያኔ ተጽእኖ ስር ሙሉ በሙሉ ወድቀው፤ የጉጅሌው ሹማምንት ሙስናና ምዝበራ ጣራ ነክቶ ባለበት በዚህ ጊዜ ፋሽስቱ ህወሓትና ጀሌዎቹ እለቱን ለመዘከር ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ለዝግጅቱ ማባከናቸው ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለያዩ አካባቢዎች የፋሽስቱ ወያኔ ካድሬዎች ህዝቡን በግዳጅ ወደ ዝግጅቶቱ እንዲወጡ ማስገደጃ አዘል መልዕክት ያስተላለፉ ቢሆንም ጭቁኑ ህዝብ ግን ምሬቱንና በአገዛዙ ላይ ያለውን ቁጣ በዝግጅቶቹ ላይ ባለመገኘትና እምቢተኝነቱን በማሳየት ማሳለፉ ተዘግቧል። ህወሓት መራሹ አገዛዝ ህዝቡን በቀን ሶስት ጊዜ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ግንቦት 20 የሃዘን ቀን ነው ያሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዕለቱን ዘከሩ

ከአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ግንቦት 20 ን ለመዘከር በሚል ከሁልጊዜው በተለየ መልኩ በጀት በመመደብ በየ ዩኒቨርሲቲዎች ያዘጋጀውን የምሳ ግብዣ ተማሪዎች አንመገብም በማለት ቀኑን ሙሉ የረሃብ አድማ አድርገው እንዳሳለፉ ለማወቅ ተችሏል።

የየዩኒቨርሲቲዎቹ ተማሪዎች ከጠዋት ጀምረው በጋራ የረሃብ አድማ በማድረግ [ዕለቱ የኢትዮጵያውያን የሃዘን ቀን መሆኑን በመግለጽ] እና በከፍተኛ ወጪ ተዘጋጅቶ የቀረበላቸውን የምሳ ግብዣ አንመገብም በማለታቸው የጉጅሌው ወያኔ ሆድ አደር ካድሬዎች እንደተመገቡት ተዘግቧል። በዩንቨርስቲው የሚማሩ የአገዛዙ ካድሬዎች ለቀረጻ እና ለፎቶ እንዲመች በተደረገ መልኩ የምሳ ግብዣውን እንዲታደሙ መደረጉ ታውቋል።

የረሃብ አድማ በየዩኒቨርሲቲዎች እንደሚኖር መረጃ የደረሰው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ በሆድ አደር ካድሬዎቹ አማካኝነት በተማሪዎች ላይ ጫና ለማድረግ የሞከሩ ሲሆን ተማሪዎቹ ግን የናንተን ርኩስ በአል አናከብርም! ከምግባችሁም አንቀርብም! በማለት በረሃብ አድማ ዕለቱን ማሳለፋቸው ታውቋል።

## አያሌ ኢትዮጵያዉያን ግንቦት 20 እንደገና ሲከበር ማየት እንደማይሹ በመናገር ላይ ናቸዉ

ኢትዮጵያ ዉስጥ በአራቱም ማዕዘናት የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን ከሰሞኑ በላኩልን ዜና መሰረት አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከአሁን በኋላ ወያኔ ይዞት የመጣዉ ግንቦት 20 በዐል ሲከበር ማየት እንደማይሹ በግልጽ ያሳያል። ብዙ ኢትዮጵያዉያን በተለይ ወጣቶች ግንቦት ሃያን የሚያከብሩት ወድደዉ ሳይሆን ተገድደዉ እንደሆነ ተናግረዉ ከአሁን በኋላ ግን ተገድደዉም ሆነ በሌላ በምንም መንገድ ግንቦት ሃያ የሚባለዉንና የኢትዮጵያ ህዝብ በዘረኞች ቁጥጥር ስር ወደቀበትን ቀን ማክበር ቀርቶ ማሰብም እንደማይፈልጉ ተናግረዋል። አንድ ከአዲስ አበባ በቀጥታ ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ስልክ ደዉለዉ ያናገሩን አገር ወዳድ እንደነገሩን ያነጋገራቸው አንዳንድ ዜጎች" የግንቦት20ን በአል ተገደው እንዲያከብሩ መደረጋቸውን ሲገልጹ"፣ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

# ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የዘረኞቹ ፍርደ ገምድል ፍርድ ቤት ግንቦት ሰባት ናችሁ ብሎ የከሰሳቸዉን ሰዎች ጥፋተኞች ናችሁ አለ

የቀድሞው የአማራ ክልል ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር የነበረዉና በወያኔ ዘረኝነት ተማርሮ ይህንን አስከፊ ስርዐት ለመፋለም መሳሪያ ያነሳዉን ዘመነ ካሴን ጨምሮ 10 ወጣቶች በተከሰሱበት የሽብረተኝነት ወንጀል ጥፋተኞች ናችሁ ተብለዉ የተለመደዉን የወያኔን የግፍ ፍርድ በመተባበቅ ላይ መሆናቸዉን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። አዲስ አበባ ዉስጥ እየታተመ የሚወጣዉ ሰንደቅ ጋዜጣ እንደዘገበው አቃቢ ህግ ተከሳሾች ከግንቦት ሰባት ድርጅት ጋር በህቡዕ ግንኙነት በመፍጠር፤ ኤርትራ ድረስ በመሄድ የጦር ስልጠና በመውሰድና ተልዕኮ ተቀብለው በመምጣት በጦር መሳሪያ የታገዘ የሽብር ወንጀል ሊፈፅሙ ነበር ብሎአል።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ.ም ተከሳሾች እንዲከላከሉ ሲበይን፣ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሾቹ ህገ-መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ በማሴር ከጎረቤት አገሮች ስልጠና በመውሰድ፤ የጦር መሳሪያ ግዢን በመፈፀምና የሽብር እቅድ በማውጣት በተለይም በአማራ ክልል በሚገኙ ባለስልጣናት ላይ ግድያ ለመፈፀም አሲረው መንቀሳቀሳቸውን ጋዜጣው ዘግቧል።አንደኛ ተከሳሽ ዘመነ ካሴ "በዐቃቤ ህግ ክስ ስር ከቀረቡበት ክሶች መካከል ኤርትራ ሄዶ የጦር ስልጠና ወስዶ መምጣቱን፣ መንግስት አሸባሪ ብሎ ከሰየመው የግንቦት ሰባት ድርጅት አመራሮች በተለይም ከጄኔራል ተፈራ ማሞ እና ከአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ጋር በአካል ተገናኝቶ የሽብር ተልዕኮ መቀበሉን፣ በፌስ ቡክና በተለያዩ የኢንተርኔት ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ሱዳን አያሌ ኢትዮጵያውያን ከአገሯ አስወጣች

ከዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ጋር እጅና ጓንት መሆኑ የሚነገርለት የሱዳን መንግስት የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ ሸሽተዉ ሰዳን ዉስጥ የተጠለሉትን ኢትዮጲያዉያን ማባረሩንና ወያኔ የሚፈልጋቸዉን ደግሞ እጅ እየያዘ ለወያኔ ማቀበሉን እየገፋበት መሆኑን ከአካባቢዉ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። በሱዳኗ መናገሻ ከተማ ካርቱም ዉስጥ ልዩ ስሙ ሁዳ እየተባለ በሚጠራው እስር ቤት ከ800 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሚገኙ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል 40 እስረኞች ሰሞኑን ከእስር ቤት ወጥተው ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውን ሱዳን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ገልጸዋል።

ካርቱም አካባቢ የተሰበሰቡ ከ600 በላይ ኢትዮጵያውያን ተጠርዘው ወደ አገራቸው መወሰዳቸውን እስካሁን ደረስ ኢትዮጵያ ይድረሱ አይደረሱ አልታወቀም የሱዳን ፖሊስ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ አዲስ በጀመረውን ኢትዮጵያውያንን ወደ አገራቸው የመመለስ ዘመቻ፣ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ሰዎች መሞታቸውንና ለአካል ጉዳት መዳረጋቸውን ኢትዮጵያውያን ገልጸዋል። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ከ15 አመት ላላነሰ ጊዜ በሱዳን እስር ቤቶች እንደሚገኙ እነዚሁ ኢትዮጵያውያን ገልጸዋል። የኢህአዴግ መንግስት ተቃዋሚዎችን ይቀላቀላሉ ብሎ በመስጋቱ የሱዳን መንግስት በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙና የገዢው ፓርቲ አባል ያልሆኑትን ዜጎች እንዲያስወጣለት መጠየቁ ይታወሳል። ሁለቱ አገሮች በቅርቡ በተፈራረሙት የጸጥታ ስምምነት የኢትዮጵያ ጦር እስከ ተወሰኑ ኪሎሜትሮች ወደ ሱዳን ድንበር ዘልቆ በመግባት ለጸጥታ ስጋት ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸውን ኢትዮጵያውያንን አፍኖ የመውሰድ ወይም ጥቃት የመሰንዘር ፈቃድ አግኝቷል። በአገሪቱ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ኮሚሽነር አቤት ቢሉም አጥጋቢ መልስ ለማግኘት አልቻሉም።

## ወያኔ በግፍ ባሰራቸዉ የኦሮሞ ተማሪዎች ላያ ሰቆቃ መፈጸሙን ሂውማን ራይትስ ሊግ አጋለጠ

ባለፈዉ ወር አምቦ ዉስጥ የተቀሰወሰዉን ህዝባዊ አምቢተኝነት ተከትሎ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ሰብስቦ ያሰራቸዉን በመግረፍ፤በመደብድብና የተለያ ከሰብዓዊነት ዉጭ የሆኑ ተግባራትን በመፈጸም እስረኞቹን እያሰቃየ መሆንኑን አለም አቁ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት አጋለጠ። የሰብአዊ መብት ድርጅቱ ባወጣው መግለጫ ከእስር ቤቶች የሚወጡት መረጃዎች አስደንጋጭና አሳሳቢ ናቸው ብሏል።

እስረኞቹ እጆቻቸውን ወደ ሁዋላ ታስረው ከሌሎች እስረኞች ጋር እንዳይገኖኙ በማድረግ የተለያዩ ማሰቃያዎች እየተፈጸሙባቸው እንደሆነ የሚገልጸው የሰብአዊ መብት ሊግ፣ አስከፊ የተባለ ስቃይ ከደረሰባቸው 10 ተማሪዎች መካከል ተማሪ ተስፋየ ቱፋ እና ባናቱ ሃይሉ ይገኙበታል።በምእራብ ወለጋ የተያዙ 50 እስረኞች የደረሱበት ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ግንቦት 20- የመከራ የስደትና ዘረኝነት አዲስ ምዕራፍ መጀመሪያ

ወያኔ ለንግሥና የበቃበትን ግንቦት 20 ቀን 1983 ዓመተ ምህረት መታሰቢያ በአል ለ23ኛ ጊዜ ለማክበር ሰሞኑን ደፋ ቀና ሲል ሰንብቷል። በኢትዮጵያ ግብር ከፋይ ህዝብ የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙሃንና በተለያዩ የውጪ አገራት የተመደቡ የወያኔ ቆንስላ ጽ/ቤቶች በዚሁ የግንቦት 20 በአል አከባበር ሥራ ተጠምደው ከርመዋል። ለኢትዮጵያ አገራችንንና ለህዝቦቿ ባርነትን ለህወሃትና ለግብረ አበሮቹ ደግሞ አልመውት የማያውቁትን ድሎትና ብልጽግናን ያጎናጸፈው ግንቦት 20 በየአመቱ ሲዘከር ልብ ልንላቸው ከሚገቡ በርካታ ትሩፋቶቹ ጥቂቶቹ ማስታወስ ይችላል፡-

1. ኢትዮጵያ አገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከአብራኳ በተገኙ ከሃዲዎች መዳፍ ውስጥ ወድቃ ሉአላዊነቷና አንድነቷ የተናጋበት ሁኔታ መፈጠሩ፤
2. በዘመናት ጥረት የተቋቋመው ህብረ ብሄር የአገር መከላኪያ ሠራዊታችን ፈርሶ በምትኩ ለጠባብ የዘውግ ጥቅም የተሰባብሰቡ መንደርተኞች ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠሩት ተቋም መመስረቱ፤
3. በከፈሉት የህይወት መስዋዕትነት አገራችንን ከውጪ ጠላት ተከላክለው ነጻነት ያወረሱን ጀግኖች አባቶቻችን ታሪክ እየተብጠለጠለ በታሪካችን እንድናፍር መደረጉ፤
4. ዜጎች በብሄር ማንነታቸው ከመንግሥት ሥራና የግል ይዞታ የሚፈናቀሉበት ዘመን መፈጠሩ፤
5. የመንግሥትና የህዝብ ሃብት የነበሩ የንግድና የአገልግሎት መስጫ ተቋሞች በሙሉ ወደ ህወሃት የግል ይዞታነት መዛወራቸው፤
6. የዘር የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት መስፈርት የሆነበት ሥርዓት ተቋቁሞ ዜጎች እርስ በርስ የሚላተሙበት፤ ለዘመናት በሰላም ከኖርበት ቀያቸው በነቂስ የሚፈናቀሉበት ሁኔታ ደጋግሞ መከሰቱ፤
7. በልማትና እድገት ሥም ሰፋፊ የእርሻ መሬቶቻችን ለህንድ፤ ለቻይናና ለአረብ ከበርቴዎች በመቸብቸቡ የነገው ትውልድ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውስጥ እንዲወድቅ መንገዶች መመቻቸታቸው፤
8. በሚሊዮን የሚጠጉ ለጋ ወጣቶች ተስፋቸው ተሟጦ ለአሽከርነትና ለግርድና ወደ አረብ አገር የሚፈልሱበት ችግር እየተባባሰ መምጣቱ፤
9. በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ስደትና እንግልት ሰለባ መሆናችን ወዘተ
10. ሃሳብን በነጻነት የመግለጽና የመደራጀት መብት ተጥሶ በርካታ ኢትዮጵያውያን በአስተሳሰባቸውና በአመለካከታቸው በእስር ቤት እንዲማቅቁ፣ እንዲገደሉና እንዲሰደዱ ተደርገገዋል ።

ወያኔ ሰሞኑን ባወጣው "የእንኳን አደረሳችሁ መግለጫ" *የግንቦት 20 ድል በሀገራችን ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረውን የዓፈናና የጭቆና ስርዓት የተወገደበትና በምትኩ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት የሚያስችል ፅኑ መሰረት የተጣለበት፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች በተለይ ደግሞ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት የማረጋገጥ ቁልፍ ጥያቄ ምላሽ ያገኘበትበመሆኑ ልዩ ቦታና ክብር ይሰጠዋል። የግንቦት 20 ድል ሀገራችን ተደቅኖባት የነበረውን የመበታተን አደጋ በመታደግ የኋልዮሽ ጉዞዋን በአስተማማኝ ሁኔታ በመቀልበስ ድሮ ወደነበረችው የስልጣኔ ማማዋ ለመመለስ የሚያስችል በህዝቦች ይሁንታና መከባበር ላይ የተመሰረተ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መሰረት የተጣለበት የህዳሴአችን ጮራ የፈነጠቀበት የድል ቀን ነው።" ብሏል።* ይህንን መግለጫ እንዳነበብን ወይም እንደሰማን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሰን እንድንጠይቀው ግድ ይለናል።

- በአገራችን ተንሰራፍቶ የነበረው አፈናና ጭቆና ደጋግመህ እንደምትነግረን ተወግዶአል ለማለት የአንድ ብሄር የበላይነት የሰፈነበት መከላከያ ሠራዊትህ መላው አገሪቱን በመቆጣጠር በአሶሳ፤ በአርሲ፤ በሃረር፤ በኦጋዴን፤ በጋምቤላ፤ በአዋሳ፤ በዋካ፤ በአረካ፤ በኦሮሚያ የተለያዩ ዞኖች፤ በጎንደር፤ በአዲስ አበባና በሌሎችም በርካታ ቦታዎች በሰላማዊ ዜጎች ላይ የፈጸማቸው ግዲያዎች፤ እስርና እንግልት በምን ቋንቋና መስፈርት ነው በቀድሞ ስራዓቶች ከተፈጸሙት ተሽለው የተገኙት?
- ደህንነት ሃይሎችህ በዜጎች ላይ የሚወስዱት ዘግናኝ እርምጃዎችና አብዛኛውን ህዝብ በፍርሃት ቆፈን ውስጥ የከተተው አንድ ለአምስት ጥርነፋህ እንዴት ተደርጎ ነው የሰብአዊና የዲሞክራሲ መብቶች ግንባታ ጽኑ መሠረት የሆነው
- ትናንት በበረባሶ ጫማ አዲስ አበባ የዘለቀው ወታደርህና ቤሳ በስቲን ያልነበራቸው መሪዎቹ ዜጎችን ከቄያቸው በማፈናቀል በተቀራመቱት የከተማ ቦታዎች የጦፈ ንግድና በጨበጥከው የመንግሥት ሥልጣን በተመቻቸ ዘረፋ የገነቡት የንግድ ድርጅቶች፤ ህንጻና ከአለም አቀፍ አበዳሪዎች በተገኘ ገንዘብ የተሠሩ መንገዶች እንዴት የዲሞክራሲና የልማት መሠረት ሊሆኑ ይችላሉ?
- በምስሌኔዎችህ የምታስተዳድራቸው ብሄር ብሄረሰቦች የእጅ አዙር አገዛዝህን እንፈልግም በስማችን አትነግድብን እያሉህ ከትውልድ መንደርህ ጀምሮ ነፍጥ እያነገቡ እያየህና እየሰማህ ስለየትኛው የብሄር ብሄርሰብ እኩልነትና ነጻነት ነው የምትደሰኩረው?
- ከውጭ በተገኘ የመሳሪያና የትጥቅ ድጋፍ የሰሜኑን የአገራችንን ክፍል ለማስገንጠል 17 አመት ሙሉ አገራችንን የወጋህ አንተው ሆነህ እያለህ ከየትኛው የአገር መበታተን አደጋ ነው እንደታደከን መላልሰህ እየነገርከ የምትደነቁረን?
- የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ አመት ታሪክ ነው በማለት የኩራት መሠረታችንን ስታፈርስ ከኖርክና በተለይ አዲሱን ትውልድ ታሪክ አልባ አድርገህ ካበቃህ ቦኋላ በየትኛው ዘመን ወደነበረው የሥልጣኔ ማማ ልትመልሰን ነው ባለ አዲስ ራዕይ የሆንክልን?

"ጆሮ ለባለቤቱ ..." እንዲሉ እነዚህ ጥያቄዎች ሲነሱ ወያኔ እንደለመደው "የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂዎች፤ ጸረ ሠላምና ጸረ ልማት ሃይሎች ፤ የብሄር ብሄረሰብ መብት የማይዋጥላቸው የአማራ ትምክህተኞች፤ የኤርትራ የጥፋት መልዕክተኞች፤ ሽብርተኞች" የሚሉ አራምባና ቆቦ የሆኑ መልሶችን እንደሚሰጥ መጠራጠር አይቻልም። የወያኔ ታሪክ ሁሌም የክህደት፣ የውሸት፣ የማስመሰል እና የማጭበርበር መሆኑን ሁሉም ህዝብ ጠንቅቆ የሚያውቀው ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ በየአመቱ የሚያከብረው ግንቦት 20 ደርግ የንጉሰ ነገሥቱን ዘውድ ገርስሶ ሥልጣን ከተቆናጠጠ በኋላ ተገፍቶ ከስልጣን እስከወደቀበት ዕለት ድረስ ያከብረው ከነበረው መስከረም 2 የተለየ ነው ብሎ አያምንም። ወያኔ ደርግን በሃይል ከሥልጣን የገረሰሰበትን ግንቦት 20ን በመስከረም 2 እንደተካው ሁሉ ህዝብ ለነጻነቱ የጀመረው ትግል ተጠናክሮ ወያኔን በሃይል ከሚቆጣጠረው ሥልጣን ሲያሽቀነጥረው የግንቦት 20 በአከባበርም አብሮት እንደሚያከትም ነጋሪ አያሻውም። ህዝብ በዘር በተሰባሰቡ ባንዳዎች መዳፍ ውስጥ የገባበትን ዕለት፤ ብሄራዊ ኩራቱንና ማንነቱን የተነጠቀበት ቀን፤ በገዛ አገሩ የበይ ተመልካች የሆነበትን የወያኔ የድል ቀን መልሶ የሚዘክርበት ምክንያት አይኖረውም። ወያኔ በየአመቱ የሚያከብረው ግንቦት 20ንና የድል ፍሬዎቹን ህዝብ እንደማይጋራው ግንቦት 7 ቀን 1997 ህዝብ በግልጽ ተናግሯል።

የግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና የትግል አላማ ነጻነት ናፋቂው የኢትዮጵያ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ግንቦት 7 ቀን 1997 ያስመዘገበውን ድል መልሶ እንዲቀዳጅ ማድረግ ነው። ስለዚህም ሰላም ፍትህና እኩልነት የተጠማኸው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ በገዛ አገርህ ሠርቶ የመኖር ተስፋህ ተሟጦ ለስደት በባህርና በየብስ ለማምለጥ እያኮበኮብክ ያለህ ወጣት፤ በየስፍራው የተቀጣጠለውን ህዝባዊ አመጽ ለማፈን እየተላክ ከገዛ ወገንህ ጋር ደም እየተቃባህ ያለኸው ወታደር፤ የገዥዎችን የሥልጣን ዕድሜ ለማራዘም በፖሊሲ ሃይል፤ በደህንነትና ጸጥታ ጥበቃ የተሰማራሃው ወገን፤ ግንቦት 7 የጀመረው የነጻነት ትግል እናንተንም ጭምር ከአፈናና ከጉስቁልና ነጻ ለማውጣት ስለሆነ ዛሬውኑ ትግሉን ትቀላቀሉ ዘንድ ድርጅትህ ግንቦት 7 ወገናዊ የትግል ጥሪውን ያቀርብልሃል።

የግንቦት 20 ድል መቀሌ ውስጥ የአፓርታይድ ሠፈር የገነቡ የሥርዓቱ ቅምጥሎች፤ አዲስ አበባ ውስጥ የመቀሌ ሠፈር ተብሎ የተሰየመውን ህንጻ ያሳነጹ ሌቦች፤ በጋምቤላ፤ በአፋር፤ በቤነሻንጉልና ማሃል ኦሮሚያ የእርሻ መሬት እየዘረፉ የተቀራመቱ ህወሃቶችና የጥቅም ተካፋዮች እንጂ የሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ አለመሆኑን በተግባር ለማሳየት ሁላችንም እጅ ለእጅ ተያይዘን የወያኔን የአገዛዝ ሥርዓት ከላያችን ላይ አሽቀንጥረን ለመጣል ከምንጊዜውም በላይ መነሳት ያለብን ጊዜው አሁን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ወያኔ በግፍ ባሰራቸዉ የኦሮሞ ተማሪዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አለመታወቁን ከእነዚህም መካከል 15 ቱ ሴቶች መሆናቸውን ድርጅቱ ገልጿል። ከዚሁ አካባቢ የተያዙና ወደ ማእከላዊ እስር ቤት ሊወሰዱ ይችላሉ የተባሉ የ9 ሰዎችን ስም ዝርዝርም ይፋ አድርጓል። በተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች ሰዎችን ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ይዞ ማሰርና ማሰቃየት መቀጠሉን በቅርቡ ከታሰሩት ድርጅቱ ተማሪዎቹ ያለምንም ቅደመ ሁኔታ እንዲፈቱ፣ ተማሪዎችን ማሰር፣ መግደልና ማሰቃየት እንዲቆም፣ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚቴ እንዲቋቋምና ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ ጠይቋል።

## ግንቦት 20፡ የኢትዮጵያዊያን ጠላት መሆንን የመረጠ ጉጅሌ ለስልጣን የበቃበት ታሪካዊ ቀን፤

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወርሃ ግንቦት የተለየ ሥፍራ አላት።ከወርሃ ግንቦት ግንቦት ሰባትንና ግንቦት ሃያን በተለይ አንረሳቸውም። ግንቦት ሃያ ጎጠኝነት፤ እኔ ብቻ ባይነት፤ አስመሳይነት ፤ስግብግብነት እና ሌብነት ተደምረው የወለዱት ቡድን ብሶት ወለደኝ ብሎ በትረ ስልጣኑን የተቆጣጠረበት ቀን። ብሶት ወለደኝ ብሎ ግንቦት 20 ዕለት በትረ ስልጣኑን የጨበጠው ቡድን ግንቦት ሰባት ዕለት ብዙ ህፃናትን፤ ብዙ ወጣት ሴትና ወንዶችን፤ ብዙ አረጋዊያንን ገድሎና በደም ሰክሮ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ለማዳፈን የሞከረበት ቀን። አዎን ግንቦት ሃያ የኢትዮጵያ ጠላት መሆንን የመረጠ ጉጅሌ ለስልጣን የበቃበት ታሪካዊ ቀን።

ህወሃትን ስልጣን ይዞ አገርን ሊመራ እንደሚችል የፖለቲካ ተቀናቃኝ ድርጅት አድርጎ ማየት ከስህተት ይጥላል። ስህተቱ ደግሞ ለነፃነት፤ ለእኩልነት እና ለፍትህ የሚደረገውን የትግል አቅጣጫ ያዛባል። የትግሉ አቅጣጫ እንዳይዛባ ህወሃት የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጠ ጉጅሌ መሆኑን አጥብቆ መያዝ ያስፈልጋል። ህወሃትን ከህዝብ ጠላትነት ዝቅ አድርጎ ማየት በማንኛውም መለኪያ  ስህተት ነው።

በዚህ ወቅት ጉጅሌው ህወሃት የህዝብ ጠላት መሆኑን የሚጠራጠር ኢትዮጵያዊ እውነቱን ለመቀበል የማይፈልግ፤ ለነፃነት የሚከፈለውን ዋጋ ለመክፈል የማይፈልግ ሰነፍ አልባሌ ሰው ነው። እንዲህ ዓይነት ሰነፍ ሰዎች ጉጅሌዎቹ ሠላም ያመጣነው እኛ ነን ሲሉ ያምኗቸዋል። ልማትም ከመቼውም ግዜ በላይ ለኢትዮጵያ ያመጣንላት እኛ ነን ሲሉ እውነት ነው ይላሉ። እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ ትበታተናለች ብለው ሲደነፉም ይደነግጣሉ።እንዲያውም ህወሃቶች ከሌሉ ማን አገሪቷን ሊመራት ይችላል ብለው ለመከራከር ይዳዳቸዋል።

ህወሃቶች በማንኛውም መስፈርት አገር ለመምራት ብቃት ያላቸው ቡድኖች አይደሉም። አገር የሚመራ ኃይል ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነትን ለማጥፋት ሳይታክት አይሠራም። ጉጅሌዎቹ ከተመሸጉባቸው የጎሳ ፖለቲካ ክበብ ውስጥ ሁነው ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነትን ለማጥፋት ያልፈነቀሉት ድንጋይ፤ያልቧጠጡት ዳገት የለም። ጉጅሌዎቹ የማያውቁት አንድ እውነት ግን ኢትዮጵያዊ ማንነት በፀና መሠረት ላይ የቆመ ተሸርሽሮ የማያልቅ ፅኑ ዓለት መሆኑን ነው። ግንቦት ሃያ ዕለት ስልጣኑን የጨበጠው ጎጠኛው ነፃ አውጪ ቡድን ከሃያ ዓመት በኋላም ሥሙን እንኳን ሳይቀይር *"እኔ ካልገዛኋችሁ ኢትዮጵያ ትበታተናለች"* እያለ ያሚርታል። ህወሃትን የህዝብና የአገር ጠላት የሚያሰኘው አንዱ አንጓም ይሄው  ነው።"እኔ ያልኩት ካልሆነ አገሪቷን አፈርሳታለሁ፤ የጎሳ ግጭት ተነስቶ ህዝቡ እርስ በርሱ እንዲተላለቅ አደርጋለሁ" እያለ መዛቱ። እንግዲህ *"እኔ ከሌለው አገሪቷን አፈርሳታለሁ"* የሚል ቡድን በምን መሥፈርት አገርንና ህዝብን መርቶ ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያደርሳት እንደሚችል "ህወሃቶች ከሌሉ አገሪቷን ማን ይመራታል" ብለው የሚጨነቁ ሰዎች መልሰው መልሰው ራሳቸውን እንዲጠይቁ እንመክራቸዋለን። ለማንኛውም ከግንቦት ሃያ መራራ ፍሬዎች መካከል አንዱ *"እኔ ያልኩት ካልሆነ አገሪቷን እበትናታለሁ"* የሚል ክፉና ጎጠኛ ጉጅሌ በአገራችን ጫንቃ ላይ መጫኑ ነው።

ጉጅሌዎቹ ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ ልማት አመጣንም እያሉ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ይጮኻሉ።የህወሃቶች ድንቁርና ልማትን ከሰው ልጅ ሠላምና ደስታ ይልቅ ዛሬ ታይቶ ነገ በሚጠፋ ግዑዝ ቁስ መለካታቸው ነው። ይህ ግዑዙ ቁስ ለሠው ልጆች ሠላም፤ ደስታና እፎይታ ካላስገኘ ልማት ሊባል አይቻልም። ጉጅሌዎቹ ልማትን የሚለኩት ከህዝቡ ደስታ፤ ሠላም እና የእለት ጉርሳቸውን ያለጭንቀት አግኝተው ማደር ከመቻላቸው አንፃር ሳይሆን ራሳቸው ዘርፈው ካካበቱት ሃብት አንፃር ነው። እነርሱ ዘርፈው ብዙ ሃብት ስላከማቹና ስም አጠራሩን እንኳ የማያውቁትን መጠጥ በብዙ ሺህ ብር ገዝተው መጠጣት ስለቻሉ አገሪቷ ያደገች ይመስላቸዋል። ጉጅሌዎቹ እንደሚሉት አገሪቷ በልማት ጎዳና ላይ እየተጓዘች ቢሆን ኑሮ ወጣቱ ትውልድ በአገሩ ተስፋ ቆርጦ የባእድ አሽከርና ገረድ ለመሆን ስደትን  የሚመርጥ ባልሆነ ነበር።ጉጅሌዎቹ አገሪቷን ከተቆጣጠሩ ከግንቦት ሃያ 1983 ዓ.ም ጀምሮ ከኢትዮጵያ መሰደድን የማይመኝ ዜጋ አይገኝም። መንኩሴ፤ ሼኽ፤ ፓስተር፤ ገበሬ፤ ምሁር፤ ተማሪ ሁሉም የሚሰደድባት አገር ኢትዮጵያ ነች። ግንቦት ሃያ ካተረፈልን ፍሬዎች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው የዜጎች ያለገደብ መሰደድ ነው። ልማታዊ ነን ብለው ራሳቸውን የሚጠሩት ጉጅሌዎቹ ዜጎች እጅግ አደገኛ በሆነ በርሃና ባህር ውስጥ አልፈው ከቀናቸው አሽከርና ገረድ መሆንን ለምን እንደሚመርጡ መልስ የላቸውም።

*"የኢኮኖሚ ልማት ... በሰው ልጅ ሁለንተናዊ እድገት፣ በዋና ዋና መሠረተ ልማት አቅርቦቶች፣ በአካባቢው ገበያ      በሚኖር ተወዳዳሪነት፣ በምቹ የተፈጥሮ አካባቢ (ኢንቫይሮመንት)፣ በማኅበራዊ መስተጋብር፣ በጤና፣ በደህንነት፣ በትምህርት እና በመሳሰሉ ነገሮች እድገት ማምጣትን ያካትታል።ብለው ልማትን የሚተረጉሙ ሊሂቃን አሉ።"*

የጉጅሌዎቹ ልማት በእነዚህ መሥፈርቶች ቢለካ ተስፋ በሚያስቆርጥ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አገራቸውን ጥለው የሚሰደዱ ዜጎች ብዛትና ዓይነት ደህና ምስክር ነው። የጉጅሌዎችን የህዝብ ጠላትነት ከሚያሳዩ እውነታዎች መካከል ሌላው ገፅ ይሄው ዜጎችን በሙሉ ተስፋ አስቆርጦ ለስደት የሚዳርግ ሥርዓት በአገሪቷ ውስጥ እንዲዘረጋ ማድረጋቸው ነው።

ህወሃቶች የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጡ ጉጅሌዎች ናቸው ስንል ሌላው መገለጫቸው ህዝቡን ሠላም ማሳጣታቸው ነው። ጉጅሌዎቹ እኛ ከመጣን በኋላ አገሪቷ ሠላም ወረደላት፤ የህዝቡም አንድነት ከመቸውም ግዜ በላይ ተጠናከረ እያሉ ያላዝናሉ።

በእውኑ ኢትዮጵያችን ውስጥ ሠላም አለን? ህዝቦቿስ ከመቸውም ግዜ በላይ በኢትዮጵያዊነት ስሜት አብሮ የመኖር ዝንባሌ እያሳዩ ነውን ? መልሱ ግልፅ ነው። ሠላም የለም፤ ኢትዮጵያም የዜጎቿ አገር አልሆነችም።

ከግንቦት ሃያ መራራ ፍሬዎች መካከልም ዜጎች ለዘመናት ከኖሩበት እና እትብታቸው ከተቀበረበት መንደር ውጡና ወደ አገራችሁ ሂዱ ተብለው ከነ ቤተሰቦቻቸው ሜዳ ላይ ተበትነው ማየታችን ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ቁም ነገር ነው። ጉራፋርዳ አማራ ተብሎ ለሚጠራው ዘውጌ ማህበረሰብ አገሩ ካልሆነ የአማራ አገሩ የት ነው? ከቤንሻንጉል አማሮች ውጡ ሲባሉ ኢትዮጵያዊነት ከወደየት አለ? በአዲስ አበባ አካባቢ የሚኖሩ የኦሮሞ ገበሬዎች ተፈናቅለው የትም ተጥለው የጉጅሌው አባላት እና ደጋፊዎች መሬታቸውን ሲቀራመቱ ህግ የት ደረሰ? እነዚህ ሁሉ ፈተናዎች የግንቦት ሃያ ፍሬዎች መሆናቸውን መርሳት አይገባም።

*እንግዲህ ጉጅሌዎቹ ነጋ ጠባ "ሰላማችን፤ ሰላማችን" እያሉ የሚያላዝኑት፤*

- *ዘረኝነት የፓለቲካ ሥርዓቱ መታወቂያ ሆኖ እያለ፤*
- *ኢፍትሃዊ የሀብትና የሥልጣን ክፍፍል እና ሙስና የሥርዓቱ መለያ ሆነው እያሉ፤*
- *ፍትህ ተዋርዳ ፍርድ ቤቶች ገዢዎች የሰጡት ቅጣት ማሳወቂያ በሆኑበት፤*
- *በዘርና በፓለቲካ ወገንተኝነት የተዋቀሩት የጦር ሠራዊት፣ የፖሊስና የስለላ ተቋማት ኢትዮጵያዊያንን ማጥቂያ ሆነው እያሉ፤*
- *በፓለቲካ እምነታቸውና በሀይማኖታቸው ምክንያት ታስረው ሰቆቃ እየተፈፀማቸው ያሉ ወገኖቻችን ብዛት በአስደጋጭ ፍጥነት እየጨመረ ባለበት ሁኔታ፤*
- *ሚሊዮኖች ድሀ ገበሬዎች ከይዞታቸው እየተፈናቀሉ በገዛ አገራቸው ስደተኛ የሆኑበት ሁኔታ እየተባባሰ መምጣቱን እያየን፤*
- *ኢትዮጵያዊያን ገበሬዎች ቤተሰቦቻቸውን የሚመግቡት ቁራጭ መሬት አጥተው እያለ ሰፋፊ ለም መሬቶች ለውጭ ባለሀብቶች በገፍ እየተሸጠ ባለበት ሁኔታ፤*
- *የወያኔ ሹማምንት በሀብት ላይ ሀብት እየጨመሩ ከተሞችን በሕንፃዎች ሲያሽቆጠቁጡ ዛንጋባ እንኳን አጥተው በረንዳ ላይ የሚያድሩ ዜጎች ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ መሆኑን በገዛ ዓይኖቻችን እያየን፤*
- *ከፍተኛ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ወጣቶች ለሚጠብቃቸው የሥራ እድል ባይማሩ ኖሮ ይበልጥ ተመራጭ ይሆኑ የነበረበት የመሆኑ አሳዛኝ ሐቅ እያየን፤*
- *ወጣቶች በተስፋ እጦት ከአገር ሲሰደዱ በባህር ሰጥመው አሊያም በበረሃ ንዳድ ተቃጥለው እያለቁ ባሉበት በአሁኑ ሰዓት፤*
- *አብዛኛው ሰው ቁርስ፣ ምሳና ራቱን ደርቦ "ቁምራ" እየበላ ስለ ተከታታይ ዓመታት 11.6 % ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት መስማት ግዴታ የሆነበት የጉድ አገር ሆኖ እያለ፤*
- *የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪቃና የአረብ አገራት እስር ቤቶች በኢትዮጵያዊያን ወንዶችና ሴቶች ተሞልተው እያለ፤ እና*
- *ወያኔ የሚያደርሰው ግፍ ፅዋውን ሞልቶ በፈሰሰበት በአሁኑ ወቅት ነው "ሰላማችን፣ ሰላማችን" እያሉ የሚያደነቁሩን።*

ይኸ ሁሉ ኢ-ፍትሃዊነት ባለበት ሊኖር የሚችለው ሰላም አሉታዊ ሰላም ያውም ተቃውሞን በጉልበት በመደፍጠጥ የሚገኘው አደገኛ አሉታዊ ሰላም ብቻ ነው።በጉልበት የሚመጣ አሉታዊ ሰላም ለአገራችን አይበጃትምና የወያኔን ሰላም መቃወም ተገቢ ነው። ከብዙ አገሮች ልምድ እንዳየነው አደገኛው አሉታዊ ሰላም ከመኖሩ አለመኖሩ ይሻላል። የወያኔ ሰላምም ለኢትዮጵያችን የሚበጅ አይደለም።

የግንቦት ሃያ መራራ ፍሬዎች ብዙ ናቸው።ግንቦት ሃያ የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጠ ጉጅሌ የአገሪቷን ስልጣን የተቆጣጠረበት ቀን ነው።ከዚህ ቡድን የሚጠበቅ መልካም ፍሬ የለም። ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ግንቦት ሃያ ቀን የአገሪቷን ስልጣን የተቆጣጠረው የጉጅሌው ቡድን ከህግ በታች እንዲውል ለማድረግ ትግላችንን አጠናክረን እየቀጠልን ነው። የትግላችን መዳረሻም የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጠ ቡድን መሪዎች እጅ ተይዞ ለፍርድ እስከሚቀርብ ድረስ ይዘልቃል። ይሄም ያለምንም ጥርጥር ይሆናል።

እናሸንፋለን።

*ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !*

## ሙስሊም ኢትዮጵያውያን ደማቅ የተቃውሞ አደረጉ

የማምለክ መብታችን ይከበር ብለዉ የዛሬ ሁለት አመት ከዘረኛዉ ስርዐት ጋር ትግል ማድረግ የጀመሩት ኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞች የድምጻችን ይሰማ የመፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባላት በፍትህ እጦት በእስር ቤት መሰቃየት መቀጠላቸውን በመቃወም በአዲስ አበባ በኑር መስጊድ በተደረገው ተቃውሞ በሙቶ ሺዎች የሚቆጠር ህዝብ መገኘቱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዜና ገለጸ። የተቃዉሞ ሰልፉን መሪዎች ያናገረዉ ዘጋቢያችን በላከልን ዜና መሰረትየተቃውሞው ዋና አላማ የሙስሊሙን ህዝብ ጥያቄ አንግበው በመያዛቸው በእስር እየተሰቃዩ ለሚገኙት መሪዎች ድጋፍ ለመግለጽ ነው መሆኑን ጠቅሷል።

በዘገየ ፍትህና በችሎት ድራማ እየተንከራተቱ የሚገኙት መሪዎች ሲታገሉለት እና ለእስር የተዳረጉበት አላማ የሙስሊም ህዝብ መሰረታዊ የመብት ጥያቄ አካል መሆኑን የገለጸው ድምጻችን ይሰማ፣ የእነሱ መስዋትነት ለህዝቡ የሰጡትን ቦታ፣ ለሃይማኖታቸው ያላቸውን ቀናኢነት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው ብሎአል። ሙስሊም ኢትዮጵያውያኑ" ኮሚቴው የህዝብ ነው፤ እኛም ኮሚቴው ነን፣ ፍትህ ለወኪሎቻችን " የሚሉ መፈክሮች ከፍ አድርገው በመያዝ እንዲሁም እጆቻቸውን አጣምረው በመቆም፣ የመሪዎቻቸውን ስቃይ ከመጋራት አልፈው ከጎናቸው መቆማቸውን አመልክተዋል።

የመፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባላት የፍርድ ሂደት እንደቀጠለ ሲሆን፣ እስካሁን ድረስ መንግስት አባላቱን በሽብረተኝነት ለመክሰስ የሚያስችለው ይህ ነው የተባለ ማስረጃ ሊያገኝ አለመቻሉን የፍርድ ሂደቱን የሚከታተሉ ሰዎች ይገልጻሉ። አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ የሙስሊሞችን የመብት ጥያቄ ለማዳከም መቻላቸውን አስመልክቶ በአንድ ወቅት መግለጫ የሰጡ ቢሆንም፣ ድምጻችን ይሰማ አሁንም ጠንካራ ደጋፊዎች እንዳሉት የሚያሳይ ተቃውሞ እየተካሄደ ነው።ተቃውሞው ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ አንዳንድ የክልል ከተሞችም መካሄዱን ለማወቅ ተችሎአል።

## ታፍኖ የተወሰደው የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ማእከላዊ ዉስጥ መታየቱ ታወቀ

ከአንድ ሳምንት በፊት ከትምህርት ገበታው ላይ ታፍኖ ተወስዶ የነበረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1ኛ አመት ተማሪና የአንድነት ፓርቲ አባል የሆነው መልካሙ አምባቸው በማእከላዊ ወንጀል ምርመራ እየተባለ በሚጠራዉ የወያኔ ሰቆቃ መፈጸሚያ ዉስጥ በእስር ላይ እንደሚገኝ ታወቀ።በጎንደር ምዕራብ አርማጨሆ ነዋሪ የሆነውና በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 6 ኪሎ የአካውንቲግ 1ኛ ዓመት ተማሪ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአንድነት መዋቅር ስራአስፈጻሚ አባል የሆነው ወጣት መልካሙ አምባቸው ሰኞ ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ማታ ራት ከበላ በኋላ ከዩኒቨርስቲ ግቢ ባልታወቁ ኃይሎች ታፍኖ ተወስዷል።

ወጣት መልካሙ የአካባቢው ነዋሪ እንደመሆኑ መጠን በጎንደር ስለ ሚደረገው የድንበር ማካለል የሚያውቀውን መረጃ በመስጠቱ በመንግስ ሀይሎች ክትትል ይደረግበት እና አንዳንዴም ማስፈራሪያ ይሰነዘርበት እንደነበር ለፍኖተ ነፃነት በተደጋጋሚ ይገልጽ ነበር።ተማሪ መልካሙ ሰሞኑን ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ታፍኖ የተወሰደው ከድንበር ማካለሉ ጋር በሰጠው መረጃ እንደሆነ በቦታው የነበሩ የዓይን ምስክሮች ገልጸዋል፡፡ ባለፉት ቀናት አንድነትፓርቲ ወጣት መልካሙ ያለበትን ሁኔታ ለማጣራት በዩኒቨርስቲው አካባቢ ወደ ሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ተወካዮችን በመላክ ጥረት ቢያደርግም፤ የሚገኝበት ቦታ እና ሁኔታ ሊታወቅ አለመቻሉን መግለጹ ይታወሳል። መልካሙን የሚያወቁት አብሮ አድጎቹ በሰጡት አስተያየት ከ2001 አመተ ምህረት ጀምሮ ማለትም ገና በልጅነት እድሜው የአገሬ ጉዳይ ያገባኛል በማለት የመኢአድ አባል ሆኖ መታገል እንደጀመረ ጠቅሰው፤ ሆኖም ላለፉት አመታት በደረሰበት ተደጋጋሚ እስር እና ድብደባ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለሁለት ዓመታት ለማቋዋረጥ ተገዶ እንደነበር አውስተዋል። ታስሮ ሳለ የ 50 ሺህ ብር ዋስትና ሲጠየቅ የሚከፍለው በማጣቱ የ አካባቢው ህብረተሰብ አዋጥቶ በመክፈል ከእስር እንዳስፈታው የገለጹት አብሮ አደጎቹ፤ በስንት ስቃይና መከራ ውስጥ አልፎ ትምህርቱን ጨርሶ ወደ ዩኒቨርሲቲ በገባበት ዐመት እንደገና ለተመሳሳይ መከራ መዳረጉ እንዳሳሰኛቸው ተናግረዋል።

## የፋሺስቶች ቀን በፋሺስቶች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንደሚያበላው ቃል የገባለት ቢሆንም፣ የህዝቡ ኑሮ እጅግ አሽቆልቁሎ እንደሚገኝ፣ በአንጻሩ ጥቂት የአገዛዙ ሹማምንት በሙስናና ብልሹ አሠራር ከገቢያቸው በላይ ሐብት አፍርተው ታግለንለታል የሚሉትን ሕዝብ መልሰው ፍዳ የሚያሳዩበት አፋኝ ሥርዓት በአገሪቱ መንሰራፋቱን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መናገራቸውን ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል።

በዝግጅቱ ወቅት በአዲስ አበባ ስታዲየም የተገኘው አሻንጉሊቱ ሃይለማርያም ደሳለኝ 23 አመታት የፋሽስቱ ወያኔ ጉዞ የምግብ ዋስትናችንን እንድናረጋግጥ እረድቶናል የሚል ዲስኩር ያሰማ ሲሆን፣ አሻንጉሊቱ ሃይለማርያም ይህን ይበል እንጅ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ ፕሮግራም በያዝነው አመት ብቻ ከ6 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚፈልጉ መግለጹ ይታወሳል።

## አርበኛ ዘመነ ካሴ ዘረኞች ያቀረበቡትን የሽብርተኝነት ክስ አጣጣለ

የወያኔ ከግንቦት ሰባት ድርጅት ጋር በህቡዕ ግንኙነት በመፍጠር፤ ኤርትራ ድረስ በመሄድ የጦር ስልጠና በመውሰድና ተልዕኮ ተቀብለው በመምጣት በጦር መሳሪያ የታገዘ የሽብር ወንጀል ሊፈፅሙ ነበር ብሎ ከከሰሳቸዉ ወጣቶች ዉስጥ የሆነዉ አርበኛ ዘመነ ካሴ በሌለበት የቀረበበትን የተለመደ የወያኔ የፈጠራ ክስ አጣጣለ። የግንቦት7 ህዝባዊ ሃይል የአመራር አባልና የቀድሞው የአማራ ክልል ወጣቶች ሊቀመንበር ዘመነ ካሴን ጨምሮ 10 ወጣቶች በተከሰሱበት የሽብረተኝነት ወንጀል ጥፋተኞች መባላቸውን ተከትሎ፣ ክሱን በሌለበት የሚሰማው አንደኛው ተከሳሽ ዘመነ ካሴ የቀረበበትን ክስ ሙሉ በሙሉ በዉሸት የተሞላና መሰረተ ቢስ ክስ ነዉ ብሎታል።

አንደኛ ተከሳሽ ዘመነ ካሴ "ኤርትራ ሄዶ የጦር ስልጠና ወስዶ መምጣቱን፣ መንግስት አሸባሪ ብሎ ከሰየመው የግንቦት ሰባት ድርጅት አመራሮች በተለይም ከጄኔራል ተፈራ ማሞ እና ከአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ጋር በአካል ተገናኝቶ የሽብር ተልዕኮ መቀበሉን፣ በፌስ ቡክና በተለያዩ የኢንተርኔት ግንኙነቶች ከሌሎች አባላቱ ጋር በመገናኘትና መልዕክት በማስተላለፍ ተጠያቂ " መሆኑን አቃቢ ህግ በክስ ማመልከቻው ላይ ጠቅሷል።

"ጄኔራል ተፈራ ማሞ በመፈንቅለ መንግስት ተጠርጥረው እስር ቤት ሲወርዱ ከስርአቱ ጋር ነበርኩ" በማለት ክሱን ያጣጣለው ዘመነ፣ "ጄኔራል ተፈራን እስር ቤት ውስጥ አግኝተኸዋል ከተባልኩም ስርአቱን በሃይል ለማንበርከክ ከሚታገል ድርጅት ጋር ከመቀላቀሌ በፊት ከስርአቱ ጋር እያለሁ ሊያስሩኝ ይችሉ ነበር" ብሏል፡

"አገሪቱ በሙሉ ወደ ግዙፍ እስር ቤት በተቀየረችበት ሁኔታ የእኔ መከሰስ አያስደንቅም ያለው ዘመነ፣ እኛ እየሞከርን ያለውን ከታሰርንበት ካቴና ተንፈራግጠን ራሳችን በማስፈታት ፣ ምናልባት ይህን አስረን ጥለነዋል የሚሉትን ትውልድ ሃይሉን አስተባብሮ ፈርገጥ እንዲልና የራሱን እጣ ፋንታ እንዲወስን" ለማድረግ ብሏል። የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ.ም በ 9 ኝ ተከሳሾች ላይ፣ ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ በማሴር ከጎረቤት አገሮች ስልጠና በመውሰድ፤ የጦር መሳሪያ ግዢን በመፈፀምና የሽብር እቅድ በማውጣት በተለይም በአማራ ክልል በሚገኙ ባለስልጣናት ላይ ግድያ ለመፈፀም የተከላከሉ በይን ሰጥቷል።

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተከሳሾች ማለትም ዘመኑ ካሴ፣ አሸናፊ አካሉ፣ ደናሁን ቤዛ፣ ምንዳዬ ጥላሁን እና አንሙት ይሄይስ በማህበራዊ ድረ-ገፆች ግንኙነትን በመፍጠር ተልዕኮና ትዕዛዝን በመቀበልና የሽብር ጥቃት ለመፈፀም የሚረዳቸውን የመሳሪያ ግዢ እንዲከናወን ማድረጋቸውን አቃቢ ህግ ገልጿል። "በአንፃሩ ደግሞ ከ6ኛ እስከ 9ኛ ድረስ ያሉት ተከሳሾች ደሳለኝ አሰፋ፣ ምክትል ኢንስፔክተር ሙልዩ ማናዬ፣ ጠጋው ካሳና ይህአለም አካሉ በሽብር እንቅስቃሴው ውስጥ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ እርዳታ ሰጥተዋል" የሚለው አቃቢ ህግ፣ ከተከሳሾች መካከል10ኛ ተከሳሽ ሆና ጉዳዩዋን ስትከታተል የቆየችው ሙሉ ሲሳይ በነፃ እንድትሰናበት ተደርጓል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ -ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## አያሌ ኢትዮጵያዉያን ግንቦት 20 እንደገና ሲከበር ማየት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

**ሌሎች ደግሞ በአሉ** ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ምድር ተከብሮ ማየት እንደማይፈልጉ ገልጸዋል።

ጠ/ሚ ሃይለማርያም ደሳለኝ የግንቦት 20 ድል የመግብ ዋስትናችንን እንድናረጋግጥ እረድቶናል ያሉ ሲሆን፣ አገሪቱ በ1983 ዓም ታመርት ከነበረው 50 ሚሊዮን ኩንታል የግብርና ምርት ወደ 250 ሚሊዮን ኩንታል መሸጋገሩዋን ገልጸዋል። አቶ ሃይለማርያም ይህን ይበሉ እንጅ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ ፕሮግራም በያዝነው አመት ከ6 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል።በአሉ በሚከበርበት በአዲስ አበባ ስታዲየም የተገኙት አቶ ሃይለማርያም ፣ ከግንቦት20 በሁዋላ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ሚሊየነሮችና ቢሊየነሮች መፈጠራቸውንም ገልጸዋል። እነዚህ ሚሊየነሮች የየትኛው ብሄር እና የየትኛው ስርዓት ደጋፊ መሆናቸውን አልተናገሩም።

የኢህአዴግ ባለስልጣናት በግንቦት20 በርካታ ድሎች የተመዘገቡበት እንደሆነ ቢገልጹም ዜጎችና የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች ግን የግንቦት 20ን ድል አጣጥለውታል። አንዲት እናት ኢህአዴግ በመጪው ምርጫ ካሸነፈና በሚቀጥለው አመት ግንቦት20ን የሚያከብሩ ከሆነ እራሴን አጠፋለሁ ሲሉ ለኢሳት ገልጸዋል። በሀረር ከተማ የሚኖር ሌላ ወጣት ደግሞ ህዝቡ ሳይፈልግ እየተገደደ ሰልፍ እንዲወጣ መደረጉን ተናግሯል። መንግስት በአሉን ለማክበር ካለፉት ሳምንታት ጀምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ማፍሰሱን መረጃዎች ያሳያሉ።

በአዲስ አበባ ብቻ በአንድ ቀበሌ ብቻ ለሻማ፣ ጧፍ፣ ባንዲራ መስቀያ እንጨት፣ መፈክሮች፣ ለለስላሳ መጠጦችና እሸግ ውሃ፣ ኩኪስና ቆሎ፣ለትራንስፖርት እና ለመሳሰሉት ወጪዎች እስከ 5 ሺ ብር የሚደርስ ገንዘብ ሲወጣ፣ በክፈለ ከተማ ደረጃ ለሚደረጉ ስብሰባዎች ደግሞ ለአዳራሽ ኪራይ ከሚወጣው እስከ 15 ሺ ብር ከሚደርስ ገንዘብ ጀምሮ፣ ለኬክ፣ ለውሃ፣ ሻሂና ቡና አቅርቦቶች የሚወጡት ወጪዎች እጅግ ከፍተኛ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ። በአገር አቀፍ ደረጃ ለበአሉ ወጪ ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ እንደሚወጣ ግምቶች የሰፈሩ ሲሆን፣ ገዢው ፓርቲ የብሄር ብሄረሰቦችን ቀን በጅጅጋ ለማክበር ካወጣው ወጪ ጋር ሲተያይ የዘንድሮው የግንቦት 20 በአል በብዙ እጥፍ ይበልጣል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የተለያዩ ፓርቲዎችና የሲቪል ድርጅት መሪዎች የግንቦት ሃያ በዐልን አከባበርና ግንቦት ሃያ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዉያን ላይ ይዞት የመጣዉን መከራና ፍዳ  በተመለከተ የሚሰጡት  አስተያየት እንደቀጠለ ነዉ። እንደ ብዙዎቹ ፓርቲ መሪዎች አገላለጽ ግንቦት ሰባት ለኢትዮጵያዉን የመጣ ሳይሆን በኢትዮጵያዉያን ላይ የመጣ የክፉ ቀን መገለጫ ነዉ ብለዉታል። የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የአንደኛው ክፍል ሊቀመንበር የሆኑት ጄል ከማል ገልቹ እንደተናገሩት የግንቦት20 በአል የኢትዮጵያ ህዝብ ከአንድ አስከፊና አንባገነን ስርአት ወደ አስከፊ፣ አንባገነንና ዘረኛ ስርአት የተሸጋገረበት ነው ብለዋል። ጄኔራሉ ግንቦት20 ከኢትዮጵያ ታሪክ፣ ልምድና ምኞት አብሮ የማይሄድ ዘረኛ መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረበት አሳዛኝ ቀን ነው ሲሉ አክለዋል።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንትና የቀድሞው የአንድነት ፓርቲ ሊ/መንበር ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እንደተናገሩት ደግሞ ግንቦት 20 የደርግ አሰቃቂ ስርአት ወድቆ ዲሞክራሲያዊ ህዝባዊ መብት የተከበረባት፣ አንድነቷንና ሉአላዊነቱዋን የበለጸገች አገር እንዲመሰረት ሙከራውየተጀመረበት ቀን ነው ያሉት ዶ/ር ነጋሶ፣ ህገመንግስት የተረቀቀ ቢሆንም፣ በ23 አመት ውስጥ ብዙ ተጀምረው ወደ ሁዋላ የተመለሱና ያልተሰሩ ስራዎች መኖራቸውን ተናግረዋል። ህገመንግስት መረቀቁንና ብሄሮች ራሳቸውን ማስተዳደር መጀመራቸው እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት እንደ ትልቅ ነገር የሚታይ ቢሆንም፣ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ አሁንም ያልተሟሉ ነገሮች አሉ ብለዋል።

ኢህአዴግ መራሹ ሃይል ደርግን በመደምሰስ የህግ የበላይነትና ዲሞክራሲን አሰፍናለሁ ብሎ ህገመንግስት ቢያረቅም፣ ኢህአዴግ በወረቀት የሰፈረውን ለመተርጎም ከደርግ የማይተነሳስ አፈናና ጭኮናና መፈጸሙን የገለጹት ደግሞ ታዋቂው ፖለቲከኛና የህወሃት ታጋይ የነበሩት አቶ አስገደ ገብረስላሴ ሲሆኑ፣ ከጥይት ጩኸት አለመላቀቃችንን፣ ሰብአዊ መብቶች አለመከበራቸውን ገልጸዋል። ከፊውዳሊዝም አስተዳዳር በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በመሬት ጉዳይ ላይ ጭሰኛ መሆኑን የገለጹት አቶ አስገደ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን አፈና ዘርዝረው አቅርበዋል ከፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ጋር የተደረገው ሙሉ ቃለምልልስ በሌላ ዝግጅት ላይ እንደሚቀርብ ለመግለጽ እንወዳለን።

## የዘረኞቹ ፍርደ ገምድል ፍርድ ቤት ግንቦት ሰባት ናችሁ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ግንኙነቶች ከሌሎች አባላቱ ጋር በመገናኘትና መልዕክት በማስተላለፍ ተጠያቂ " መሆኑን ገልጿል።

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተከሳሾች ማለትም ዘመኑ ካሴ፣ አሸናፊ አካሉ፣ ደናሁን ቤዛ፣ ምንዳዬ ጥላሁን እና አንሙት ይሄይስ በማህበራዊ ድረ-ገፆች ግንኙነትን በመፍጠር ተልዕኮና ትዕዛዝን በመቀበልና የሽብር ጥቃት ለመፈፀም የሚረዳቸውን የመሳሪያ ግዢ እንዲከናወን ማድረጋቸውን አቃቢ ህግ ገልጿል። “በአንፃሩ ደግሞ ከ6ኛ እስከ 9ኛ ድረስ ያሉት ተከሳሾች ደሳለኝ አሰፋ፣ ምክትል ኢንስፔክተር ሙልዩ ማናዬ፣ ጠጋው ካሳና ይህአለም አካሉ በሽብር እንቅስቃሴው ውስጥ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ እርዳታ ሰጥተዋል” የሚለው አቃቢ ህግ፣ ከተከሳሾች መካከል 10ኛ ተከሳሽ ሆና ጉዳዩዋን ስትከታተል የቆየችው ሙሉ ሲሳይ በነፃ እንድትሰናበት ተደርጓል። ተከሳሾች ከመጪው ሰኔ 17 እስከ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በተከታታይ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ ወንጀል ችሎት እንዲያቀርቡም መታዘዛቸውን ጋዜጣው ዘገባውን አጠቃሏዋል። ዘመነ ካሴ የተከሰሰው በሌለበት ሲሆን ወጣቱ የግንቦት7 ህዝባዊ ሃይል የአመራ አባል መሆኑ የሚታወስ ነዉ።